ፓኖራማ ቁጥር 49

የትዝብት አድማስ

ጥቅምት 28 2001 ዓም

# <u>በአንዲት ሀገር አንድ ባላ</u>

ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራው ሀገራችን፥ ተፈጥሮ ከአደላት መሠረታዊና ዓይነተኞች ፀጋዎች መካከል የመጀመሪያውና ዋናው የዜጎቿ ጉራማሌነት መሆን ለክርክር የሚቀርብ አይደለም። በዜጎቻቸው ጉራማይሌነት የሚቀናባቸው ሌሎች ሀገሮችም ቆጥራቸው በርከት ያለ ነው። ሌሎች ሀገሮች የሚቀናባቸው በጉራማይሌነታቸው ብቻ ሳይሆን፥ ይህን በተፈጥሮ ያገኙትን የዜጎቻቸውን ጉራማይሌነት የብሔራዊ መለያ ጉልላትና የሀገራቸውም አንድነትና ጥንካሬ ምልክት አድርገው ስለሚመኩበት ነው። በልዩነታቸው አንድነታቸውን በአንድነታቸው ደግሞ፥ ጥንካሬያቸውንና ኃያልነታቸውን ስለሚያረጋግጡ፥ ጉራማይሌነታቸውን፥ ለመበታተንና ለመፈረካከስ ምክንያት ለማድረግ አይጠቀሙበትም። በመሆኑም፥ከአንድነትና ከጥንካሬ ከተገኘ ታላቅነት፥ሥልጣኔያቸውንና ብልፅግናቸውን ለኑሯቸው መሠረት ያደርጉታል። በአንድነት ጥንካሬን ያገኛሉ እንጅ በልዩነት ድክመትንና ድህነትን አይጋብዙም ። የድክመትና ድኅነት ምንጫቸው ጭቆና፥ ፍትኀ-ርትዕ ማጣትና የፍርድ መጓደል በመሆናቸው፥ ጭቆናንና ብዝበዛን አስገዶ በዴሞክራሲ ሥርዓት መተዳደር የመኖራቸው ዋስትና መሆኑን በሚገባ ይገነዘቡታል። ይህም በመሆኑ የተለያዩ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ያሏቸው ሀገሮች፥ ዜግነታቸውን ለኩራትና ለአንድነት የሚጠቀሙበት ሁሉም ተስማምተው በጋራ በመሰረቱት ሥርዓተ መንግሥት ስለሚተዳደሩ ነው።በዚህ መሠረታዊ ስምምነትና መግባባት የተነሳ፥ የቋንቋ ፥ የዕምነት፥ የባኅል፥ የዘርና የመሳሰሉት ልዩነቶቻቸውን አቻችለውና አቀራረበው፥ ተከባብረውና ተስማምተው በጋራ ከመኖር በቀር ሌላ ምርጫ አይኖራቸውም።

ኢትዮጵያ ሀገራችንም ከዚህ የተሻለ ምርጫ ሊኖራት ስለማይችል ዜጎቿን በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማስተዳደር የኀልውናዋና የአንድነቷ፥ የጥንካሪዋና የብልፅግናዋ መሠረት መሆኑን ማንም ዜጋ ሊክደው አይችልም። አይገባምም። እኛም፥ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደመታደል ሆኖላት የብዙ ብሔርና ብሔረሰቦች ሀገር በመሆኗ የዜጎቿን ጉራማሌነት እንደ ፀጋ ከማይትና ለታላቅነቷ መሠረት ከማድርግ የበለጠ ሌላ ምርጫ ሊኖራት አይገባም ብለን በፅኑ እናምናለን። ይህም ሲባል፥ የተለያየዩ ብሄሮቿ ለዘመናት ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ አድርገው ያቆይዋት መሆናቸውን ማንም ሊክደው ባይችልም በታሪክ ሂደት በተለያዩ ሥርዓተ-ማኀበራትና ሥርዓተ-መንግሥታት የተለያዩ ጭቆናዎችና ብዝበዛዎች አልተፀሙባቸውም ብሎ በዛሬ ጊዜ ደፍሮ የሚናገር ዜጋ ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም። በተለያዩ ዜጎቿ ላይ

የሃይማኖት፥ የባኅል፥ የብሄር፥ የፆታ፥ የመደብና ሌሎችም ጭቆናና በደል ተፈፅሞባቸዋል ብሎ ማስመዝገብ፥ ለሀገራችን መሠረታዊ ችግሮች መፍተሄ ለማምጣት የመጀመሪያው ርምጃ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

የስድሳ ስድስቱ የካቲት ሕዝባዊ አመፅም የሁሉም ዜጋ አመፅና ሮሮ እንጅ በተለይ ለአንድ ወይም ለተወሰኑ የኅብረተስብ ክፍሎች ብቻ አንጡራ ሀብት፥ ጥያቄና አመፅ አልነበረም፡፡ ይህን መሠረታዊና ታሪካዊ ሀቅ ለማሽመድመድም ይሁን አቅጣጫ ለማሳት ወይም አሁን የቀጠለውን ብሄራዊ ሕዝባዊ የነፃነት ትግል ለመሸራረፍና ለማምታታት ብሎም ሕዝባዊ ኃይሉን ለመከፋፈል ሆን ተብሎ የሚደረግ ሴራ፥ ለማንም አይጠቅምም፡፡ ለአንዲት ኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ አርነት በሚደረገው ትግል፥ እኔም ትገሬ ነኝ፥እኔ ደግሞ ኦሮሞ ነኝ ፥ ጉራጌ ነኝ፥ አማራ ነኝ እያሉ ማቀንቀን፥ነኝ ለሚሉት ብሄርም ይሁን ለመላዋ ኢትዮጵያ የሚጠቅም አይሆንም፡፡ ይህን ሊሉ የሚችሉ፥ የብሔር ድርጅት አባል ሆነው ብሎም፥ ብሄራቸውን ነፃ እናወጣለን የሚሉ ክፍሎች ቢሆኑ፥ ምናልባት ሳያስደንቅ ይችል ይሆናል፡፡ በሁሉን አቅፍ ድርጅት ስር ተደራጅተው ለመላው ኢትዮጵያ አርነት የሚታገሉ አባላት ግን፥ይህንን የመሸራረፍ አዝማማሚያ ሲታዘቡ፥ ድርጊቱን በአርምሞ የሚያልፉት ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም የዚህ ዓይነቱ አዝማሚያና አካሄድ በጊዜው ካልተቀጨና ካልተስተካከል፥ወዴት አቅጣጫ እንደሚያመራና ምንስ ሰበብ እንደሚያስከትል መገመት ካባድ አይሆንም፡፡ ሰው ያልበላውን ማከክ ከጀመረ፥ አካሉን ከመምለጥ በቀር የሚያገኘው ጠቀሜታ አይኖረውም፡፡ማንም ዜጋ ሀሳቡን በፅሁፍም ይሁን በነባቢት የመገለፅ መብቱ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ እንዳማይችል ሁሉ፥ይህን ሰብዓዊ መብት መከታ በማድረግ ሀገራዊ ትግሉን ጥላሸት ለመጨመር በሚርደርገው ማቀንቀን፥ ከመቀንቀኑ አስቀድሞ ይህንን የሚያደርገው ክፍል ሁለት ጊዜ እንዲያስብ ይጠበቅበታል፡፡
"በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ" እንዲሉ፥መብትን ከግዴታ፥ ነፃነትን ከኃላፊነት ጋር እያመሳከሩ፥ እያጣጣሙና እያጣቀሱ ካልተሄደ በስተቀር፥ በእንዝህላልነትም ይሁን በትዕቢት ወይም በዕቅድ የሚነገሩትና የሚደረጉት ድርጊቶች ሁሉ የሚያስከትሉትን የአጭርና የረዥም ጊዜ አሉታዊ አንደምታዎች ለማረም ያስቸግራል፡፡ የአጋንንትን በረት መክፈት፥ የኋላ ኋላ ማጣፊያው የሚቸግር ይሆናል፡፡ እዛም ቤት እኮ፥ እሳት አለ እንዲሉ! የአንድን ሀገር ዜጎች፥በነጣላም ይሁን በቡድን ለመጉዳት ማንም የሞራል ሥልጣንና ተልዕኮ እንደሌለው ሊታወቅ ይገባል፡፡

ማንም ይሁን ምን፥በተለያዩ ምክንያቶችና መንስዔዎች፥ይህንን የመላዋን ኢትዮጵያንና የዜጎቿን ብሔራዊና ስትራተጂያዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚታገለውን የአይበገሬ ትውልድ ትግል፥ ለመከፋፈልና ለመሸራረፍ፥ብሎም አቅጣጫውንም ለማሳት የሚደረገው ደባ ከየትኛውም አቅጣጫ ይሰንዘር መቃወምና ማጥቃት፥ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት የቆመው ዜጋ ሁሉ ኃላፊነትና ግዴታ ነው፡፡ እስካሁንም ድረስ ትግሉ እንደዚህ እየተሽመደመደና እየተጥመለመለ ያለው፥በቁርጠኝነት ማን ምን መሆኑ ሳይታወቅ ሁሉም በጅምላና በደፈናው ስለሚፈረድና ስለሚፈረጅ ነው፡፡ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ

***ጥቅም ብቻ የቆመውን ኃይልና  በሌላ በኩል ደግሞ፥ ለየብሄሩ ጥቅም መቆም የመጀመሪያ አጀንዳው አድርጎ የተሰለፈውን አንጠርጥሮና አበጥሮ ማወቅ፥ ወቅታዊ የትግል ግንዛቤ ሊሆን ይገባል፡፡***

***በሀገራዊው የኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ግንባር ዣንጥላ  እየተጠለሉና በአሳሳች የኢትዮጰያ መፈክር ስር ከሌላው ጋር ስመሳይ መፈክር እያቀነቀኑ፥በተጨባጭ ግን የየራሱን ብሔር ባላ በመመርኮዝ ሲፈፀም የነበረው ጮሌነትና ክህደት ማክተምና መጋለጥ አለበት፡፡ ለኢትዮጵያ ሀገራቸው ብሔራዊ ጥቅም በመቆም የሚዋደቁት ሀገር ወዳድ አርበኞች፥ከሀገራቸው ብሔራዊ አጀንዳ በስተቀር ሌላ አጅንዳ የላቸውም፡፡ የትግላቸው ዓላማና መንፈስ እንዲሁም የመጨረሻ ግባቸው ለኢትዮጵያ ጥቅም እየተዋደቁ መሰዋት እንጅ ሌላ ቀዳማይም ይሁን ዳሃራይ ዓላማ  የላቸውም፡፡ ለብሔራቸው ጥቅም ብቻ እንደቆሙት ክፍሎች፥ እንደ ሁኔታውና እንደጊዜው አመችነት የተለያየ ባላ በመመርኮዝ፥አንዱ ባላ ሲሰበር በሌላው እየተንጠለጠሉ የፖለቲካ ዘማዊነት መፈፀም የሚቻል አይሆንም፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ!***

 ***ቀደም ሲል የነበረውን የትግል ተመክሮ ለጊዜው ወደጎን በመተው፥ ወያኔ አዲስ አበባ ከገባበት ከአለፉት አስራ ስምንት ዓመታት  ውስጥ በተካሄደው የኅብረት መስረታ ሙከራ የተደረገውን  የተቃዋሚ ድርጅቶችን ሁኔታ እንኳን ልብ ብሎ ለተገነዘበ አስተዋይ ዜጋ፥አብዛኛዎቹ የብሄር ደርጅቶች ወደ ኅብረት ምሥረታ ጉባዔ ሲሄዱ የነበሩት፥"አይተነው ጊዜ ወደ አደላበት" በሚል በከፊል ልብ በተመላ የእበላ ባይነት ሂሳብ እንደነበረ ለማንም ግልፅ ነው፡፡ይህ ሁኔታ፥ በዕውነት ከልባቸው አምነውበትና የተቃዋሚ ድርጅቶች መተባበር ለሀገር ግንባታ ይጠቅማል ብለው ተግተው ሲሰሩ የነበሩትንና ሀገራዊ አጀንዳም የነበራቸውን/ያላቸውን ኅብረ ብሔር ድርጅቶችን ጎድቷቸዋል፡፡ ጊዜአቸውን፥ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን አባክኖባቸዋል፡፡እንዲያው በደፈናው ለኅብረት ምስረታ የተደረጉት ጥረቶች ሁሉ ከንቱ ነበሩ ለማለት ባይቻልም፥ የተደረጉት ሙከራዎች ግን ከጥቅማቸው ይልቅ ያለመጥቀማቸው ያዘነብላል ለማለት የሚቻል ይመስላል፡፡ እዚህ ላይ ሕብረት ይጠቅማል/አይጠቅምም ወደሚል የአፍርሳታ ጉንጫ አልፋ  ልውውጥ ለማምረት ሳይሆን፥ ከእንግዲህ ወዲህ ሕብረት ያስፈልጋል ከተባለ፥ሕብረት ለምን? ከማንስ ጋር? መቼ? እንዴት? ወዘተረ.. የመሳሰሉትን መሪ ጥያቄዎች ጠይቆ ትክክለኛውን መልስ ከማግኘቱ በፊት፥እንዲያው በግብታዊነት ስለ ሕብረት ማውራት ከንቱ መሆኑን ለመጠቆም ነው፡፡***

***እስካሁን ድረስ ሕብረት አግኝተናል ሲባል የነበረው የፌዝ አነጋገር ሁሉ ሊያስታውሰን የሚችለው ተመክሮ ቢኖር፥ " የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል" የሚለውን የቆየ ይትብሃልን ነው፡፡ይህ ደግሞ ለሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት የፖለቲካ መርህና አሰራር የሚጠቅም አይደለም፡፡ <u>ከዚህም በቀር ለሕብረት ተካፋይ በመሆን እየመራንም ከግብ እናደርሳለን እያሉ ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት የሕብረቱንም ጅማሮ ሂደት ከወያኔ ጋር መደራደሪያ በማድርግ ሲጠቀሙበት የነበሩ የብሄር ድርጅቶች፥ በኢትዮጵያ የፖለቲካ</u>***

ትግል ውስጥ በፖለቲካ የመገለባበጥ ችሎታቸውን ያስመሰከሩበትና እንደ እስስት የመለዋወጥ ባኅሪያቸውን ያሳዩበት መሆኑንም ለማስታወስ ብለን ነው።

ይህ ትዝብት ወደፊት እንደ አስገራሚ ተመክሮ ተወስዶ፥በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ድራማ ፥ ማን? ምን? ሚና እንደሚጫዎት ታውቆ፥ በሕዝብና በሀገር ላይ የሚቀልደውም ተለይቶ፥ ወያኔን በእርግጥ አምርረው የሚፋለሙትን ወገኖች ብቻ በመለየት ሀገራችንን አሁን ካለችበት የጥፋት ፀድፍ ማውጣት ይዋል ይደር የሚባል ጉዳይ መሆኑን ማወቅ ወሳኝ ነው። ለዚህ ውሳኔ እንዲረዳ የሚከተሉት ግንዛቤዎች ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል።

1. ወያኔዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ በጎሳ በመከፋፈል የራሳቸውን ጠባብ ብሄረተኛ አጀንዳ ለማራመድ የተጫወቱት የጎሳ ካርድ በአሁን ጊዜ እየከሸፈ መሄዱን መገንዘብ ያስፈልጋል። በመሆኑም፥ የትግራይ ሕዝብ አደጋ እያንዣበበት ነው የሚል አንደምታ ያለውን መልዕክት ማስተላለፍ፥ የወያኔ መሪዎች ሲጠቀሙበት ለነበረው፥ግን አሁን የከሸፈ የጎሳ ካርድ ነፍስ መዝራት እንዳይሆን መጠንቀቅና ለነመለስ ዜናዊ የፕሮፖጋንዳ ማገዶ ማቀበል እንዳይሆን ማስተዋል ያስፈልጋል። ምን ጊዜም ቢሆን፥ ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ጠላቶቹ የወያኔ መሪዎች እንጅ የደሙ ፍሳሽ፥የአጥንቱ ቁራጭ የሆነው የትግራይ ሕዝብ እንዳለሆነ መታወቅ አለበት።

2. ይህ በመካሄድ ላይ ያለው የብሔራዊ ነፃነት ትግል እክል እንዳይገጥመውና ብሎም ትግሉን ለመሸራረፍና ለመገነጣጠል የሚከጅለውን ማነኛውንም አዝማሚያ በቀጥታም ይሁን በአንደምታ እንዳያንሰራራ ነቅቶ በመጠበቅ አስፈላጊውን ርምጃ ሁሉ መውሰድ፥

3. ኢትዮጵያን ነፃ ሊያወጧት የሚችሉት በሁሉትና በሦስት ባላዎች የሚንጠላጠሉ አስመሳይ የብሔር ድርጅቶች ሳይሆኑ፥ ለኢትዮጵያ ዘለቄታ ጥቅም በመቆም ስትራተጂያዊ አጀንዳቸው የሀገራቸው መዳን ብቻ መሆኑን አምነው ከወያኔ ጋር የሚዋደቁትና ማንነታቸውም በትግል ያስፈተኑ እውነተኞቹ ቆራጥ ታጋዮች በቻ መሆናቸውን በመቀበል፥ ከእነዚህ የነፃ አውጭ አርበኞች ጋር መተባበርና መርዳት፥

4. የሀገራችን ብሄራዊ የነፃነት ትግል የመጨረሻው ዓላማና ግቡ፥መላውን የሀገሪቱን ዜጎች ለጋራ ነፃነትና ብልፅግና፥ፍትኀ ርትዕና ዕድገት እንዲሁም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማብቃት ነው።ይህንን ታላቅ ሀገራዊ ተልዕኮ ተግባራዊ ለማድረግ፥ያልተከፋፈለ፥ያልተሸራረፈና ያልተፍረከረከ ትግል ማካሄድ ወሳኝ መሆኑን ከልብ ማመን ያስፈልጋል።

**በመጨረሻም፤ መሬት ከፍ ሰማይ ዝቅ ቢል ፥ኢትዮጵያ ሀገራችን የዜጎቿን እኩልነትና አንድነት በመጠበቅ በነፃነቷ ለዘለዓለም እንደምትኖር፥ቅንጣት ያህል ብዥታ አይኖረንም። ልብ ያለው ልብ ይበል!!!**